# ዲያስፖራው ህብረተሰብ በአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ፣ በኮንስትራክሽን፣ ኢንዱስትሪ እና በቤት ልማት ዘርፎች ሊሳተፉና ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉባቸው መስኮች

ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር

መጋቢት 20/2003 ዓ.ም.

<u>አዲስ አበባ</u>

## የዲያስፖራ ህብረተሰብ በአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ፣ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪና እና በቤት ልማት ዘርፎች ሊሳተፉና ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉባቸው መስኮች

በሀገራችን ባለፉት ዓመታት የተገኘውን ከፍተኛና አበረታች የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረት በማድረግ በከፍተኛ የዕድገት አማራጭ 14.9 በመቶ እንደሚደርስ በመገመት በተለይም የልማት ዕቅዶችን ለማሳካት የሚጠይቀውን ፋይናንስ ለማሟላት እንዲችል ዲያስፖራው ቁጠባን በማሳደግ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ሊሰማራ እንደሚችል ታሳቢ የተደረገ ሲሆን በውጭ አገር ያሉ ዜጎቻችን በሀገራቸው ውስጥ በምርትና በአገልግሎት ዘርፍ እንዲሳተፉ ካሉት ምቹ ሁኔታዎች መካከል:-

- የሀገሪቱ ሕዝብ ከ80 ሚሊዮን በላይ መሆንና ሰፊ የሀገር ውስጥ ገበያ መኖር ፣
- የሀገሪቱ ዕድገት በተከታታይ በዓመት ሁለት አሐዝ መሆኑና መድረሱና በተለይ የገበሬው ምርት ማደግና ገቢ መሻሻል፣
- የከተሞች ዕድገትና ብዛት በሰፊው መጨመር የሕዝቡም የአመጋገብ፣ የአለባበስና የኑሮ ሁኔታ በመለወጥ ላይ መሆኑ፣
- የመግዛት አቅም ያለው ገበያ በቅርብ ርቀት መኖር /መካከለኛው ምስራቅ ወዘተ.../ ተጠቃሽ ናቸው:: በመሆኑም በአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ፣ በኮንስትራክሽን ዘርፍ እና በቤቶች ልማት ዲያስፖራው ሊሳተፍባቸው የሚችሉ ሥራዎች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል::

### I.በአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ዘርፍ ሊሳተፍና ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉባቸው መስኮች

### 1. የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ

- በጨርቃጨርቅና አልባሳት በተለያዩ የሽመና፣ የፋብሪካ ጨርቆች ፣ የተዘጋጁና ለምዕራቡ ዓለም በቀለምና በወቅት ፍላጎት ተስማሚ ሆነው የሚዘጋጁ ልብሶችን ማቅረብ ይችላል:: ለዚህም የሀገር ውስጥ አቅርቦት /ጥሬ ዕቃ/ የማመቻቸት ዕዱሉ ሰፊ ነው፣
- የቆዳ ውጤቶች ምርት በተለይ በጫማና በጫማ ሶል ፣ በቆዳ ቦርሳ፣ ሻንጣ ፣ የስፖርት ትጥቅና ሠፊ ገበያ ሊያስገኙና የጥሬ ዕቃ አቅርቦቱም በሀገር በማደግ ላይ ያለ ነው፣
- የሹራብ ምርቶች፣ ካልሲዎችና የሹራብ ክሮች በሀገር ሊመረቱ የሚችሉና ከውጭ በመግባት ላይ ያሉትን መተካት የሚችሉ ከመሆናቸውም ሌላ ገበያውም ገና ያልዳበረ በመሆኑ ሰፊ የገበያ ዕድል ይጠብቀዋል::

- የተለያዩ የብርድ ልብስ ዓይነቶች ፣ ጃንጥላዎች ፣ በስፋት ከውጭ በመግባት ላይ ያሉና በሀገር ውስጥ ሊመረቱ የሚችሉ ናቸው፡፡

## 2. በምግብና መጠጥ ዘርፍ

- ጥሬ ዕቃዎች /ቦለቄ፣ ሽንብራ ፣ ምስር ፣ አተር.../ በማዘጋጀት በእሽቱ በማሸግ ቢቀርብ /ከገበሬ ጋር በተቀናጀ አሠራር / ሰፊ ገበያ ይኖረዋል፡፡
- አትክልትና ፍራፍሬ አቅርቦት እያደገ በመሄድ ላይ በመሆኑ በምርቱ ላይ እሴት በመጨመር /በማዘጋጀት ፣ በመጭመቅና በማሸግ/ ማቅረብ፣
- ቡና፣ ቅመማ ቅመም፣ ማር፣ ቲማቲም በተለያዩ መልክ በማዘጋጀት በማሸግ ለገበያ ማቅረብ፣
- የባህል መጠጦችን በዘመናዊ መልክ በማጣራት ፣ በቀመምና በማሸግ ማቅረብ፣
- የታሸጉ የጤፍ ዱቄት ፣ የቆሎ ፣የበሶ፣የዳቦ ቆሎ፣ የቺፕስ፣ የአዋዜ ወዘተ...ማዘጋጀት ለገበያ ማቅረብ፣
- የተለያዩ የከረሜላ ፣ የቸኮሌት ፣የማስቲካ ምርቶችን በማመረት የገቢ ምርቶችን መተካት፣

## 3. በከተማ ግብርና ዘርፍ

- ዘመናዊ የወተት እርባታ በማከናወን የተለያዩ የወተት ተወፅኦዎችን ለገበያ ማቅረብ፣
- ዘመናዊ የዶሮ እርባታዎችን በማካሄድ ሰፊ የገበያ ዕድልን በሀገር ውስጥና ለአካባቢ አገሮች ማቅረብ፣
- በከተሞችና በገበሬው አካባቢ ለሚካሄደው የእንስሳት እርባታ የሚያገለግል የእንስሳት መኖ አዘጋጅቶ ማቅረብ፣
- ዘመናዊ ሆቴሎችና በከተማው ሕብረተሰብ ተፈላጊ የሆነው የእንጉዳይ ምርት አምርቶ ማቅረብ /በተለይ ለአዲስ አበባ/

## 4. ለትምህርት ሥራ የሚውሉ ቁሳቁሶች ምርት

- የተማሪዎች ቦርሳዎች /ከሸራ ፣ ጨርቅ ፣ፕላስቲክ ናይለን / የተሰሩ በማምረት እያደገ የመጣውን ፍላጎት ማሟላት፣
- የትምህርር መሣሪያዎች ቁሳቁስ እርሳስ፣ ላጲስ ፣ መቅረጫ ፣ማስመሪያ ፣ኮምፓስ ፣ ደብተሮች ፣ ፓዶች ፣ ፎልደሮች አዘጋጅቶ ማቅረብ፣

5. **የቱሪስት መስሕቦችንና ባህላዊ እሴቶችን የሚያስተዋወቁ ምርቶች**

- ባህላችንን፣ ኑሮአችንን ቅርሶቻችንን የሚያስተዋውቁ ከጨርቅ፣ ከነሐስ ፣መዳብ፣ ብር ፣ ወርቅ፣ እንጨት ፣ ፕላስቲክ የሚሰሩ ቁሳቁሶች ምርቶች /መስቀሎች፣ የሙዚቃ መሣሪያዎች ፣ ሐውልቶች /
- በቅርፃቅርጽና በአሸንጉሊት መልክ የሚዘጋጁ ፣ የእንጨት ፣ የጨርቅ ምርቶች፡
- ባህላዊ የብሔር ብሔረሰብ ልብሶችን በዘመናዊ ጥበብ በማዘጋጀት የሚቀርቡ ቱሪስት ቁሳቁሶች፣

6. **የእንጨት ሥራ ዘርፍ**

- የቀርከሃ ምርትን በተያዩ የቤት፣ የቢሮና ፣ የሕንፃ አገልግሎት ምርቶች በመቀየር ለገበያ ማቅረብ፣
- ከውጭ የሚገቡ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች በማምረት መተካትና ለሀገር ገበያ ማቅረብ ፣
- የእንጨት ማሽኒያና በጣበቂያ ሙጫዎችን ማምረትና ገቢ ምርቶችን መቀነስ፣
- በደን ተከላ በመሳተፍ ለጣውላ ፣ ኮምፒልሳቶ ፣ ችፑውድ የሚሆን ማምረትና ማዘጋጀት፣

7. **ለገበሬው የሚያገለግሉ መሣሪያዎችና መገልገያዎች**

- ለመስኖ አገልግሎት የሚውሉ አነስተኛ ሞተሮችን መፈብረክ ወይም መገጣጠም ፣
- በየገጠሩ ሊተከሉ የሚችሉ የእህልና የበርበሬ ወፍጮዎች ፣ማበጠሪያዎች መፈብረክ ፣
- ለመስኖ አገልግሎት የሚውሉ ፕላስቲክ ፓይፖችን ማምረት፣
- ለግብርና ሥራ የሚያገለግሉ የምርትና የትራንስፖር መሣሪያዎች /ማረሻዎች ፣ጋሪዎች.../ ማምረት፣

8. **የመአዛ ዘይት የማዘጋጀት ሥራ**

- ለሽቶ እና ለውበት ማስዋብያ የሚሆኑ የመዓዛ ማምረት፣
- ለምግብ ጣዕምና ለመድሀኒት የሚሆኑ የመአዛ ዘይቶችን ከገበሬው ጋር በማቀናጀት ማምረትና ጨምቆ ማቅረብ፣

9. **የውድቅዳቂ ወይም የተራፊ ምርት ሥራዎች**

- ከውድቅዳቂ ፕላስቲኮች፣ ወረቀቶች፣ ጨርቃጨርቅና ጠርሙስ ...ወዘተ ምርቶችን መልሶ ማምረትና በዚያውም የከተሞችን ንጽሕና መጠበቅ፣

## 10. የወርክሾፕ አገልግሎቶች

- ከፍተኛ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ጥገና አገልግሎት፣
- metal casting, metal treatment, galvanizing ,electroplating, foundry ሥራዎች በጣም ተፈላጊና ገበያ ያለው እንደሆነ ይታመናል፣
- የተለያዩ ማሽኖች በተመለከተ የዳቦ መጋገሪያ ፣ የድንጋይ ወፍጮዎች፣Mixers, Vibrators, የሚገቡ በከፍተኛ ደረጃ የሚመጡ በመሆኑ በሀገር ውስጥ ለማምረትና ለመተካት የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ ይሆናል ሰፊ ገበያም ይኖረዋል።

## II. በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ ቢሳተፉ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉባቸው መስኮች

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለዕድገት አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ረቂቅ ሠነድ የተዘጋጀና የሕንጻ አዋጅ ወጥቶ በአሁኑ ጊዜ የሕንፃ ደንብ እንዲፀድቅ እየተደረገ የሚገኝ በመሆኑ ዲያስፖራው በኮንስትራክሽን ዘርፍ ሊሳተፉባቸው የሚችሉ ሥራዎች

- በተለያዩ የግንባታ ዘርፎች በሥራ ተቋራጭነት መሳተፍ፣
- ከፍተኛ አቅም በሚጠይቁ ግንባታዎች ላይ በልዩ ልዩ ሙያ በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት መሳተፍ፣
- በመንገድ ፣ በባቡር ፣ በመስኖ ወዘተ...ባሉ የግንባታ ዓይነቶች ላይ በአማካሪነት መሳተፍ፣
- የሀገራችን የኮንስትራክሽን እንዱስትሪን ለማሳደግ በተለያዩ ወጪ እና ጊዜ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች ሽግግር እንዲፈጠር ማድረግ፣
- በኢንዱስትራ ውጤቶች እና የአካባቢ ግብዓት ምርትና አቅርቦት፣
- የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን /ዶዘር ፣ ግሬደር፣ ሎደር  ወዘተ .../ በማስገባት በኪራይ እንዲውሉ በማድረግ፣
- የውጭ ባለሐብቶችን በኮንስትራክሽን ዘርፉ በመሳብ በጋራ በመሆን ኢንቨስት ማድረግ ፣
- የኮንስትራክሽን ዘርፍ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚጠቀም በመሆኑ በውጭ ምንዛሬ አቅረቦቱ መሳተፍ፣
- ለግንባታ ሥራ የሚያገለግሎ የስኳር ፕሮፖስ አቅርቦትና የኪራይ አገልግሎት፣
- ለግንባታ በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኘውን ኮንክሪት ባቺንግ ፕላንት በማምጣት ኮንክሪት ማምጣት፣

## III. በቤት ልማት ዘርፍ ሊሳተፍና ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉባቸው መስኮች

- በውጭ ምንዛሪ 40 በመቶ የቅድሚያ ክፍያ በማድረግ በቀሪ 60 በመቶ የባንክ ብድር ትስስር የቤት ባለቤት መሆን፣
- በግልና እና በህበር በመደራጀትና ገንዘብ በመቆጠብ የቤት ባለቤት መሆን፣
- ለመኖሪያ እንዲሁም ለምርትና አገልግሎት መስጫ ስራዎች በተዘጋጁ ቦታዎች ቤት ለመገንባት የሚያስፈልግ መሬት በሊዝ ጨረታ ማግኘት፣
- በቤት ልማት ለስራ ተቋራጮችና ለአማካሪዎች በሚደረገው የክህሎት፣ የካፒታል ፣ የመሳሪያና ማሽነሪ አቅም ማሳደጊያ ትስስር ተጠቃሚ መሆን፣
- ለቤቶች ልማት እና ትስስር ባላቸው የመንግሥት ፕሮጀክቶች በሚያስፈልጉ የኢንዱስትራ ውጤቶች የሆኑ የአርማታ ብረት፣ የሳኒተሪና የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ፣ የሴራሚክስ ውጤቶች ፣ የአካባቢ ግብአቶች የሆኑ ጠጠር አሸዋና ድንጋይ ፣ እንዲሁም ፕሪፋብሪኬትድ የሆኑ በስታንዳርድ የተሰሩ በርና መስኮቶች ፣ ለጣሪያና ኮርኒስ የሚሆኑ ማቴሪያሎች ምርትና አቅርቦት መሳተፍ፣
- ለቤቶች ልማት እና ትስስር ባለቸው የመንግሥት ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉ ማሽነሪና ተሽከርካሪ አቅርቦት እንዲሁም የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት በመስጠት መሳተፍ፣
- በሪል እስቴት የቤት አልሚነት መሳተፍ፣
- በአምስት አመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሰረት በቤቶች ልማት ፕሮግራም እና ልዩ ልዩ የመንግሥት ግንባታ ፕሮጀክት ፣በስኳር ልማት ቤቶች ግንባታ በአዲስ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም በዕቅዱ ተይዞ በሚገኘው በማዳበሪያ ቤቶች ግንባታ በአማካሪነት ድርጅት ፣ በሥራ ተቋራጭነት በመሆኑ ወይም በባለሙያነት በመቀጠር የሥራ ትስስር ማግኘት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡